# የኢትዮጵያ የሰብዓዊነት የሀገር ውስጥ ቡድን (HCT)
# መሪ መርሆዎች
# በትግራይ ውስጥ እንዲሁም በአፋር እና አማራ ክልሎች ድንበር አካባቢዎች ለሚደረጉ ሰብዓዊ ተግባራት የሚያገለግሉ

## የጸደቀበት ቀን ህዳር 2020

## 1. መግቢያ

የአንድን ሀገር በክልሉ ውስጥ ወይም በቁጥጥሩ ስር ያሉ ሰዎችን ፍላጎቶች የመጠበቅ እና የማሟላት መደበኛ እና ተፈጥሮአዊ ሃላፊነት እውቅና በመስጠት

ተቀባዩ መንግስት በተባበሩት መንግስታት ቻርተር እና የተባበሩተ መንግስታት ሰራተኞች ደህንነት እና ጥበቃ፣ በተባበሩት መንግስታት የደህንነት አስተዳደር ስርአት(UNSMS) የሚሸፈኑ ግለሰቦች፣ እና የተባበሩት መንግስታት የደህንነት አስተዳደር ስርአት ድርጅቶቸ ንብረቶች ደህንነት ከሌሎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች ጋር በተገቡ ተዛማጅ ስምምነቶች መሰረት ልዩ ሃላፊነት እንዳለበት መገንዘብ፣

የሰብዓዊ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ያሏቸውን ስራዎቻቸውን በሰብዓዊነት መርሆዎች ፤ ሰብዓዊነት፣ አለማዳላት፣ ገለልተኝነት፣ እና የትግበራ ነጻነት መሰረት ለመስራት ያላቸውን ቁርጠኝነት እንደገና ማረጋገጥ፣ [1]

ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊነት ስራ ሰብዓዊ ድጋፍን ከታች በተጠቀሱት የሰብዓዊነት መርሆዎች መሰረት በግጭቶች መሃል እና ከግጭቶች በኋላ በውጤታማነት እንዲያከናውን ለመምራት ያልማል፡፡

## 2. መሪ መርሆዎች

### 2.1 የሰብዓዊነት መርሆዎች

**አለማዳላት እና ሰብዓዊነት** (በሰብዓዊነት መርህ መሰረት)፡ህይወትን ለማዳን ፣መከራን ለማቅለል እና የሰብዓዊነትን ክብር ለመጠበቅ እና (ባለማዳላት መርህ መሰረት) ድጋፍ በእጅጉ ለሚያስፈልጋቸው የትም ቢሆኑ እና ያለልዩነት መድረሱን ለማረጋገጥ ሰብዓዊ ድርጅቶች የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለባቸው፡

- ማንነትን፣ ጎሳን፣ የፖለቲካ አመለካከትን፣ ጾታን፣ ብሄርን፣ ዘርን ፣ ወይም ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ መድልዎ አለመኖሩን በማረጋገጥ የተጎጂ ሰዎችን ፍላጎቶች አስመልክቶ ግልጽ፣ ወቅቱን የጠበቀ፣ እና ነጻ የሆነ ፍተሻ ማከናወን መቻል አለባቸው። እንደዚህ ስራ አንድ አካል፣ በግጭት ውስጥ ያሉ ሁሉም አካላት ቴሌኮሙኒኬሽን የሰብዓዊ ድጋፍን የማስተባበር እና የማቅረብ ስራን ለማመቻቸት ያለውን ጠቀሜታ እንዲሁም በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ከቤተሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመጠበቅ እና ወደነበሩበት ለመመለስ መገናኘት እንዳለባቸው መገንዘብ አለባቸው፡፡ ያለ ቴሌኮሙኒኬሽን ሰብዓዊ ሰራተኞች ያለችግር እና ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ መንቀሳቀስ እና በችግር ላይ ያሉ ሰዎችን መደገፍ ስለማይችሉ ሁሉም ወገኖች ቴሌኮሙኒኬሽንን ላለመገደብ መወሰን አለባቸው።

---

1. [1] ለተባበሩት መንግስታት የማስተባበር ድጋፍ እነዚህ መርሆዎች ከተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ 46/182 (ታህሳስ 10 1991) እና 58/114 ( ታህሳስ 2003) የተወሰዱ ናቸው፡፡ እንዲሁም የሰብዓዊ ድርጅቶችን የሚመሩ የስነምግባር ደንቦች እና የድርጅታዊ ተልዕኮ መግለጫዎች ክፍል የሆኑም አሉ ፡፡

- የተባበሩት መንግስታት ወይም የተወከሉ ኤጋሮች የተጠቃሚ ዝርዝሮችን በገለልተኛነት ማረጋገጥን ተከትሎ በኢትዮጵያ መንግስት እና በተባበሩት መንግስታት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ፍላጎቶች ለመለየት የጋራ መመሪያዎችን ይተግብሩ እንዲሁም ድጋፍ የሚቀርበው በፍላጎቶች ላይ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ በየምዝገባ እና ስርጭት በሚካሄድባችው ስፍራዎች የጥበቃ ዕርዳታ ዴስኮችን ያቋቁሙ እና ሌሎችንም ዘዴዎች ይጠቀሙ፡፡

- በኢትዮጳያ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1110/2019 መሰረት ስደተኞች አገልግሎቶችን (የጤና ክብካቤ፣ የህግ ድጋፍ ወዘተ.) ማግኘት አለባቸው፡፡

እነዚህ መመሪያዎች አንድ ችግር ውስጥ ያሉ ሲቪሎች የሚገኙበትን አካባቢ ማናችውም ስልጣን ያለው ሃይል ይቆጣጠረው ሰብዓዊ ድርጅቶችን በግልፅ ፣ በተጠያቂነት እና በተጣጣመ ሁኔታ ፍላጎትን የመለየት መንገድ እንዲሁም ሰዎችን ያማከለ ፣ ጥበቃ ተኮር እና ፣ በማስረጃ ላይ የተመሠረተ አካሄድን እንዲጠቀሙ ይደግፋሉ ፡፡ ለተጎዱ አካባቢዎች ድጋፍን የሚያቀርቡ ሁሉም ሰብዓዊ ድርጅቶች፣ መንግስትን፣ የተባበሩት መንግስታትን፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ እነዚህን ደረጃዎች እንዲያሟሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በችግር ላይ ያሉ ሰዎችን የመለየት ስራ የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎች ያከብራል ፡

- *ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አሰራር በመጀመሪያ ድጋፍ እና ጥበቃ በጣም ለሚያስፈልጋቸው እና ለችግር ተጋላጭ ለሆኑት (በትክክል በተደነገጉ መመዘኛዎች መሠረት) ገለልተኛ በሆነ የማረጋገጫ ሂደት ይደረጋል ፤*
- *አለማዳላት የመለየት ስራ የሚሰራው በግጭት የተጎዱ ሰዎች መካከል (የተፈናቀሉ ቢሆኑ ወይም ሌላ) ስደተኞች፣ ከስደት ተመላሾች ፤ ሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የተጎዱ እና ተቀባይ ማህበረሰቦች፣ ተመላሽ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ወደሌላ ስፍራ የተዛወሩ ወይም በአካባቢ የተቀናጁ ተፈናቃዮች፣ አካቶ ማንነትን፣ ጎሳን፣ የፖለቲካ አመለካከትን፣ ሀይማኖትን፣ ጾታን፣ የጾታዊ ፍላጎት ዝንባሌን ወዘተ ያደረገ ልዩነት ወይም መድልዎ በሌለበት መንገድ ነው፡፡;*

- *በሰብዓዊ ድርጅቶች እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል የተቀናጀ አካሄድ፤*
- *ተጠያቂነት ለተጎዱ ህዝቦች፡ የተጎዱት ማህበረሰቦች ትርጉም ያለውና አካታች ተሳትፎ እና መረጃ መስጠት ፍላጎቶች በሚለዩበት ጊዜ ሁሉ ይረጋገጣል፤*
- *ግልጽነት ፡ ሰብዓዊ ድርጅቶች ከሁሉም አካላት ጋረ ግልጽ በሆነ መንገድ ይሰራሉ እናም ለሚረዷቸው ተጠያቂነት አለባቸው፡፡*
- *ተሳትፎ፡ የመለየት ስራ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በሂደቱ ውስጥ የተጎዱትን የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ በተከታታይ ይፈልጋል ፡፡ የተሳትፎ መንገዱ እና መጠኑ አውዱን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡ ሰብዓዊ ድርጅቶች ፍላጎቶችን እና ተጋላጭነቶችን ለመለየት ለቤተሰብ የሚደረጉ ቃለ መጠይቆች፣ የትኩረት ቡደን ውይይቶች እና/ ወይም ስብሰባዎችን ይጠቀማሉ፡፡*

**ገለልተኝነት እና ነጻነት** ፡ የሰብዓዊ ድጋፍ ሰብዓዊ ስራ በሚተገበርባቸው አካባቢዎች (ከነፃነት መርህ ጋር በሚስማማ መልኩ) ማንኛውም ተዋናይ ሊይዛቸው ከሚችሉ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ወታደራዊ ወይም ሌሎች ዓላማዎች ገለልተኛ መሆን አለበት እንዲሁም በግጭት ውስጥ ወግኖ መሄድ ወይም የፖለቲካ ፣ የዘር ፣ የሃይማኖት ወይም የርዕዮተ ዓለም ተፈጥሮ ያላቸው አለመግባባቶች ውስጥ መግባት የለበትም (ከገለልተኝነት መርህ ጋር በሚስማማ መልኩ)።

የሰብዓዊ ድርጅቶች ተግባራት በየትኛውም የግጭቱ ክፍል አለመሳተፋቸውን ያረጋግጣሉ እናም በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሰብአዊ አቅርቦቶችን እና አገልግሎቶችን መስጠት ላይ ብቻ ያተኩራሉ ፡፡ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ፣ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ እና በአለም አቀፍ የስደተኞች ሕግ መብቶች መከበር የገለልተኝነትን መርህ አይቃረንም ፡፡ የሰብዓዊነት ሰራተኞች የሚሰጧቸው ድጋፎች ሁሉ በተጠቃሚዎች የፖለቲካ ፣ የሃይማኖት ወይም የርዕዮተ ዓለም አመለካከት ላይ የተመሰረቱ አለመሆናቸውንም ያረጋግጣሉ ፡፡ የሰብዓዊነት ሰራተኞች በሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች የፖለቲካ፣ የሀይማኖት፣ ወይም የርእዮተአለም ተጽእኖ አለማሳደራችውንም ያረጋግጣሉ።

የሰብዓዊነት ሰራተኞች የሰብዓዊ ድርጅቶችን ገለልተኝነት ለማቃለል የሚያልሙ መግለጫዎችን (በማህበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁትን አይነት) ከመተቸት ወይም ከመደገፍ ይቆጠባሉ። ሁሉም አካላት ግምታዊ መግለጫዎች ፣ መጣጥፎች ወዘተ የሰብአዊ ሠራተኞችን ሕይወት እና የሚያገለግሏቸውን ማህበረሰቦች ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥሉ መሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው ::

ዕርዳታን መጠቀሚያ የማድረግ አደጋን ለማስቀረት እና የሰብአዊነት ሰራ ነፃነትን ለማረጋገጥ ፣መንግስት በራሱ ቁጥጥር ስር ወዳይደሉ ግጭት ያለባቸው ግዛቶች ጭምር የሰብአዊ ሰራተኞች በፍጥነት እና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መድረስ መቻላቸውን ያረጋግጣል።

ሁሉም አካላት በሰብዓዊ ተግባራተ ወቅት ትክክለኛውን እና የሚታወቀውን ገለልተኝነት እና ነጻነት እንዳይጣስ በሰብዓዊ ሰራተኞች እና ወታደሮችን፣ የጸጥታ አካላትን፣ የፖሊስ ባለስልጣናትን እና ማንኛውም ሌሎች የታጠቁ ቡድኖችን ጨምሮ ባሉ በታጣቂ ቡድኖች መካከል ያለውን ልዩነት ማስጠበቅን ልብ ሊሉ ይገባል። የሰብዓዊ ድጋፍ የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች የታጠቀ አጃቢን አይጠቀሙም የሰብአዊነት የሀገር ውስጥ ቡድን (ኤች.ሲ.ቲ.) የታጠቀ አጃቢን እንደ ‹የመጨረሻ አማራጭ› ለመጠቀም ካልወሰነ በስተቀር ይህም በተባበሩት መንግስታት የደህንነት አስተዳደር ስርዓት ውስጥ በተደነገገው መደበኛ የደህንነት ስጋት ግምገማ ሂደት የተረጋገጠ ከሆነ ነው ::

### 2.2. ሌሎች መርሆች እና አቀራረቦች

**ክብር፡** በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች በተግባር በሁሉም እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደ መብት ባለቤቶች እና እንደ እኩል አጋሮች ሊከበሩ ይገባል እንዲሁም በሁሉም ተግባቦቶች ውስጥ እንደ ሰው ክብራቸው መጠበቁ ይደግፋል ::

የሰብዓዊነት አጋሮች የተጎዱ ስዎችን በእኩል ደረጃ እንዳሉ አጋሮች በፍላጎቶች የመለየት ስራ ፣ መርሃግብር ነደፋ፣ ክትትል እና ግምገማ የማካተት ጥረታቸውን መጨመር አለባቸው:: የተጎዱ ሰዎች በሰብዓዊነት ሰራ ውስጥ ቀጣይነት ባለው እና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ የሰብዓዊነት ስራ ማእከል ላይ መቀመጥ አለባቸው:: የሰብዓዊነት ሰራተኞች የማህበረሰብ ተሳትፎ በሚቻለው ደረጃ እንዲኖር በአሰራሩ ሁኔታ የሚቻሉትን ሁሉ ማድረግ እንዲሁም በሚቻልበት ስፍራ ሁሉ ግብረ መልስ እና የቅሬታዎች መቀበያ ዘዴንም እንዲኖር ማድረግ አለባቸው ።

**ከወሲብ ብዝበዛ እና በደል መጠበቅ**: ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመከላከል፤ ለማጋለጥ እና ለመዋጋት በሰብዓዊ ድርጅቶች ሰራተኞቻቸው ወሲባዊ ብዘበዛን እና በደልን የመከላከል ግዴታቸውን ማወቃቸውን እና ማክበራቸውን በማረጋገጥ ንቁ ጥረቶች መደረግ አለባቸው ::

**ምንም ጉዳት አለማደረግ :** ሰብዓዊ ድርጅቶች ሰራዎቻቸው ሊረዷቸው የሚፈልጓቸው ሰዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያሳድሩ እና ለግጭት የሚዳርጉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ድጋፍ ለመስጠት በሚገኙበት ጊዜ እና በሚሰጡበት ጊዜ 'ምንም ጉዳት ላለማድረግ' መጣር አለባቸው :: ይህም ማለት፣ ድጋፍ የሚደረግላችው ሕዝቦች ሊደርሱባቸው የሚችሉ አደጋዎችን በመመርመር ዒላማዎች አለመደረጋቸውን ማረጋገጥ ወይም ድጋፍ እና አገልግሎቶችን በመቀበል ተጨማሪ የጥበቃ አደጋ እንዳጋጠማቸው ማረጋገጥ ነው::

## 3. መርሆዎችን በስራ ላይ ማዋል

የተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ ድርጅቶች እና አጋሮቻቸው የሰብዓዊ ጥበቃ እና ድጋፍ ስራዎችን እንዲሰሩ የሚከተሉት የአሰራር ሁኔታዎች ወሳኝ ናቸው:

- የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት እና ሌሎች በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት የሚመለከታቸው ሲሆን ለችግረኞች ሁሉ ፍላጎቶችን ለመዳሰስ፣ ድጋፍ ለመስጠት፣ መብቶችን ለመጠበቅ እና የሰብዓዊ ተግባራትን ለመከታተል እንዲያስችል ወቅታዊ ደህንነቱ የተጠበቀ ያልተገደበ እና ዘላቂ የሰብአዊ ድርጅቶች ተደራሽነትን ማመቻቸት አለባቸው ::
- እንደ መድሃኒት፣ ክትባት፣ ምግብ፣ የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦቶች፣ መጠለያ፣ የውሃ የአካባቢ እና የግል ንጽህና እና ጥበቃ ቁሳቁሶች ያሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች እና የአስፈላጊ አቅርቦቶች ዝውውር ሊስተካከል እና ሊጠበቅ ይገባል::

ባለሥልጣናቱ ሁሉም የተጎዱ ሕዝቦች አስፈላጊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማስቻል ህጋዊ ሰነዶችን ማመቻቸት እና ማቅረብ አለባቸው ። እንደ ምሳሌ፣ ከዚህ በፊት በነበሩ ክስተቶች ቀበሌዎቻቸው የምዝገባ ሰነድ ስላልሰጧቸው የተፈናቀሉ ሰዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ የጤና አገልግሎቶች መጠቀም አይችሉም ነበር።

- የኢትዮጵያ የጸጥታ ሀይሎች ፣ የደህንነት ማጣሪያ ሲያደርጉ ማጣሪያ የሚደረግባቸው ሰዎችን የሲቪልነት ሁኔታ ለማረጋገጥ እንዲሁም እንደ የስነልቡናዊ እና ማህበራዊ ድጋፍ፣ ቤተሰብ ማፈላለግ ፣ ክትትል ማድረግ/ የህክምና ሪፈራል ወዘተ መኖራቸውን ለማረጋገጥ የተባበሩት መንግስታት እና አለም አቀፍ ቀይ መስቀል መሳተፍ ይኖርባቸዋል።
- እንዲከበሩ እና ከማናቸውም ትንኮሳ ፣ ማስፈራራት ወይም የዘፈቀደ እስር እንዲጠበቁ ለሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ የሰብዓዊ ሰራተኞች የሚሰጥ ማረጋገጫ እና ቁርጠኝነት።

ሰብዓዊ ድርጅቶች ስራዎቻቸውን ሲሰሩ ፡

- ችግር ውስጥ ላሉ ሰዎች ፈጣን እና ያልተገታ የሰብዓዊ አገልግሎት እንቅስቃሴ ፣ ድጋፍ ፣ ጥበቃ፣ እና አገልግሎት መስጠት እንዲቻል የሰብዓዊ ድጋፎች በሚፈለጉባቸው አካባቢዎች ከሚገኙ አካላት እና የሚመለከታቸው ተዋናዮች ጋር መተባበር
- የሰብዓዊነትን መርሆዎች ለማክበር እና ለማስተዋወቅ እንዲሁም አለም አቀፍ ህግን ለማክበር የሚረዱ ግልጽ የጋራ የሆኑ የአድቮኬሲ መልዕክቶች ለሁሉም አካላት መድረሳቸውን ማረጋገጥ።
- በመርህ የሚመራን የሰብዓዊነት ስራ እና ውጤታማ የማስተባበር ስራን ለመመስረት እና ለመጠበቅ ከመንግስት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች፣ የአካባቢ ባልስልጣናት፣ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ወዘተ ጋር በማስተባበር ስልቶች መተባበር።
- የታቀዱ የሰብዓዊ ተግባራትን አስመልክቶ ለመንግሰት፣ ለአካባቢ ባለስልጣናት እና የሚመለከታቸው ሲሆን ለሌሎች አካላት ተገቢ መረጃ መስጠት፣
- ለአድቮኬሲ እና ሃብት ለማሰባሰብ እንዲረዳ የተጎዱ ሰዎችን ሁኔታ ፣ የተለዩ የሰብዓዊ ፍላጎቶች፣ እና የታቀዱ የሰብዓዊ ተግባራት፣ አስመልክቶ ለሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ማህበረሰብ ግልጽ እና ተገቢ መረጃን ማጋራት።

ሰብዓዊ ድርጅቶች የሚከተሉትን አስመልክቶ የማንንም አካል ጥያቄ አይቀበሉም፡

- ሰብዓዊ ድጋፍ ለጫኑ ተሽከርካሪዎች የመሳሪያ አጀብ መስጠት ፤ ባለው መመሪያ መሰረት በየሰብዓዊነት ሀገር ውስጥ ቡድን እንደመጨረሻ አማራጭ ካልተወሰደ በስተቀር [2] እና ኢትዮጵያን በሚመለከቱ ሀገራትን ያማከሉ መመሪያዎች መሰረት [3] በግልጽ በተቀመጡ መለኪያዎች እና በተለዩ የደህንነት ስጋት ዳሰሳዎች መሰረት ቀድሞ ስምምነት ላየ ከተደረሰ ፤
- ድጋፍን ለታጠቁ ሀይሎች ወይም ታጣቂ ቡድኖች አባላት ጥቅም ሲባል ማድረግ፣
- መጋዘኖችን፣ ተሽከርካሪዎችን፣ ቁሳቁሶችን፣ የግንኙነት መሳሪያዎችን እና ቢሮዎችን የመሳሰሉ የሰብዓዊ ድጋፍ ንብረቶችን መያዝ፣ ጥበቃ ማድረግ እና ማስተዳደር፣
- የሰብዓዊ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቦታዎች ወይም ተሽከርካሪዎች ውስጥ የጦር መሳሪያ የዞ መግባት፤
- የተባበሩት መንግስታት እና የኢጋሮች የሰብዓዊ ድጋፍ ሰራተኞችን የግል ዝርዝር ጉዳዮች ማጋራት፣
- የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን እና የሰብዓዊ አግልግሎት መስጫ እቃዎችን እና አግልግሎቶችን ለፖለቲካ ወይም ለውትድርና አላማዎች መያዝ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማዘዝ፣

***መጨረሻ***

---

[2] የሰብዓዊ ድጋፍ የሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎችን በመሳሪያ ስለማጀብ አስገዳጅ ያልሆነ የአይ ኤስ ኤ ሲ መመሪያ፣ የካቲተ 27፣ 2013

[3] ሰብዓዊ ሲቪል - ወታደር ማስተባበር መምሪያ፣ ኢትዮጵያ፣ መጋቢት 13 2019 ዓ ም በሰብዓዊ ማስተባበሪያ ቡድን የጸደቀ